## **የ ኖቭል ኮሮና ቫይረስ ወቅታዊ ጋዜጣዊ መግለጫ**

የዓለም ጤና ድርጅት የኖቭል ኮሮና ቫይረስ በሽታ ከታሕሳስ 21, 2012 ዓ.ም ጀምሮ በቻይና ዉሃን (Wuhan) ግዛት የተከሰተ መሆኑን አሳውቋል፡፡ በድርጅቱ ሪፖርት ማሰረት ይህ በሽታ ከተከሰተበት ቀን ጀምሮ እስከ ጥር 24, 2012 ድረስ ከ 23 ሀገራት በጠቅላላ 14, 557 ታካሚዎች በቫይረሱ ማያዛቸው ሪፖርት ያደረጉ ሲሆን ከቻይና ውጪ ያሉ አገራት 146 በቫይረሱ የተጠቁ ታካሚዎችን ሪፖርት አድርገዋል፡፡ ከነ ዚህም ውስጥ አሜሪካ፣ ጃፓን፣ ታይላንድ፣ ኮሪያ ሪፐብሊክ፣ አውስትራሊያ፣ ሲንጋፖር፣ ፈረንሳይ፣ ኔፓል፣ ካናዳ፣ ማሌዥያ፣ ቬትናም፣ ካምቦዲያ፣ ፊሊፒንስ፣ ሲሪላንካ፣ ፊንላንድ፣ ህንድ፣ ጀርመን እና ዩናይትድ አረብ ኢሚሬትስ ይገኙበታል፡፡ ሌሎች የሚረጃ ምንጮች (የጆን ሆፕኪንስ ዩኒቨርስቲ የኮኖና ቫይረስ ኬዞች) እስከ ጥር 25 ድረስ በቫይረሱ ማያዛቸው የተረጋገጠ 17,373 ሰዎች የደረሰ ሲሆን 362 ታካሚዎች ህይወታቸውማለፉን ዘግበዋል፡፡

የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ከጤና ሚኒስትር እና ሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን ለኖቬል ኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ እየተወሰዱ ካሉ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ውስጥ ብሔራዊ ታስክ ፎርስ እና በኢንስቲትዩቱ ለኮሮና ቫይረስ ድንገተኛ አደጋዎች ምላሽ የሚሰጠውማዕከል ስራ ጀምረዋል፡፡ ከኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ፣ ከኦሮሚያ ክልል ጤና ቢሮ፣ ከቦሌ አየር መንገድ፣ ከግልና ከመንግስት ጤና ተቋማት ለተውጣጡተሳታፊዎች የግንዛቤ ማስጨበጫስልጠና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ተሰጥቷል፡፡ በተመሳሳይ ዛሬ ለ200 የሚሆኑ የሆስፒታል አመራሮች እና ባለሞያዎች በጤና ሚኒስተር አማካኝነት የግንዛቤ ማስጨበጫስልጠና ይሰጣል፡፡

በቦሌ ኢንተርናሽናል ኤርፖርት እና 27 የተለያዩ የድምበር መግቢያ እና መውጫኬላዎች ላይ የሚደረገው የማጣራት ምርመራ በተጠናከረ ሁኔታ እየቀጠለ ይገኛል፡፡ የማጣራት ምርመራው ከፍተኛ የሙቀት ማጠን ያላቸውን ተጓዦች የሚለይ ሲሆን ይሄም የቫይረሱ የበሽታ ምልክት የሚያሳዩትን ለማለየት ይረዳል፡፡ እስከ ጥር 24/2012 ድረስ 47,162 ተጓዦች የሙቀት ማለያ ምርመራ የተደረገላቸው ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 1,695ቱ የማጡት ቫይረሱ ሪፖርት ከተደረገባቸውሀገራት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከቻይና የሚማጡሁሉንም ተጓዦች በሀገር ውስጥ በሚቆዩበትን ግዜ፤ አድራሻ፤ እንዲሁም የተለያዩ ሚረጃዎች መዝግቦ በማያዝ እስከ 14 ቀን ድረስ የሚከታተል ቡድን ተቋቁሞ እየተከታተለ ይገኛል፡፡ ይህም ምልክት በሚያሳዩበት ግዜ ፈጣን ምላሽ ለማስጠት እና ንክኪ ያላቸውን ለማለየት ይረዳል፡፡ ፈጣን ምላሽ ሰጪቡድን (rapid response team) ተዋቅሮ የቫይረሱ ምልክቶችን ጥቆማ በተሰጠ ከ2 ሰዓት ባነሰ ግዜ ውስጥ ማጣራት እንዲችል ለ24 ሰዓት በፈረቃ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛል፡፡ ለዚህም ስራ የአየር ሚረፊያዎች ፤ ሆስፒታሎች፤ የታክሲማህበራት፤ ኢንደስትሪያል ፓርኮች እና የኮንስትራክሽን ቦታዎች የጠበቀ እይታ አግኝተዋል፡፡ ቫይረሱ አለባቸውተብሎ የሚጠረጠሩትን ታካሚዎች ህክምና ወደ ሚያገኙበት ቦታ የሚወስዱ 4 ተሽከርካሪዎች（2 ኣምቡላንሶች）ተመድበው ወደ ስራ ተሰማርተዋል፡፡ የቅዱስ ጴጥሮስ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፤ በቦሌ ጨፌ ያለው የህክምና ቦታ እና የየካ ኮተቤ ሆስፒታል ለህክምና ማስጫ ት ተመርጠዋል፡፡ የህክምና ቦታዎች የወረርሽኝ ስርጭት ለመቀነስ የታካሚብዛትን ያማከለ ሲሆኑ፤ የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል ስፔሻላይዝ ባደረገበት በጽኑ

ህሙማን እና በሳንባ ህመምዘርፍ የአርተፊሻል የሳንባ ሕክምና መርጃ መሳሪያ (mechanical ventilator) ህክምና ለማስጠት ዝግጅቱን አጠናቋል፡፡ እንዲሁም ለህክምና የሚያስፈልጉ መድሀኒቶች፤ የህክምና እቃዎች ፤ የግል ደሕንነትን ማጠበቂያ እቃዎች ( personal protective equipment) ወደ ህክምና በታዎች ተሰራጭተዋል፡፡ ህክምና ለማስጠት የሚያስችሉ ፕሮቶኮሎች እና መመሪያዎች ተሰርተዋል፡፡ በክልሎች ላይምተመሳሳይ መዋቅር እንዲደራጅ የተጠየቀ ሲሆን አንዳንድ ክልሎች ላይ የዝግጅት እና ምላሽ ስራ ተጀምሯል፡፡

ለጥቆማእና መረጃ ለማግኘት ነጻ የስልክ ማስመር 8335 ከጥር 24/ 2012 ጀምሮ የ24 ሰዓት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ እስካሁን 17 ጥቆማዎች የደረሱን ሲሆን ፤ ከነዚህም ስምንቱ በለይቶ ማቆያ ክትትል ሲደረግላቸውነበር፡፡ በኢትዮጵያምከቻይና ውሃን ግዛት የመጡእና የመተንፈሻ አካል ህመምና ከፍተኛ ሙቀት ማሳየት የጀመሩ ሁለት (2) ሰዎች እና ከእነርሱ ጋር የቅርብ ግንኙነት የነበራቸው ተጨማሪ ሁለት(2) ሰዎች ተገኝተው በለይቶ ማቆያ ማዕከል ውስጥ ክትትል እየተደረገላቸው መሆኑንና ናሙናቸውም ወደ ደቡብ አፍሪካ መላኩ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ጥር 21/2012 ዓ.ም. የምርመራ ውጤቱ የደረሰንና ሁሉም ናሙናዎች ከቫይረሱነፃ መሆናቸውየተረጋገጠስለሆነ በዚያውቀን ከለይቶ ማቆያ እንዲወጡ ተደርጓል፡፡ ይህንንምተከትሎለቤተሰቦቻቸውሲደረግ የነበረውክትትል ተቋርጧል፡፡

በአሁኑ ወቅትም አራት ሰዎች በበሽታው ተጠርጥረው ፤ አንድ ቻይናዊ እንዲሁም ሶስት ኢትዮጵያዋን፤ አንድ በአክሱም እና ሶስቱ በቦሌ ጨፌ በለይቶ ማቆያ ክትትል እየተደረገላቸውሲሆን ናሙናቸውተወስዶ ወደ ደቡብአፍሪካ ለመላክ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡

የኖቬል ኮሮና ማረጋገጫምርመራ ሪኤጀንት በአለምየጤና ድርጅት ትብብር አማካኝነት ወደ ሀገራችን በቅርቡ ይገባል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በቫይረሱ የተጠቁ ታካሚዎችን በማለየት እና አስፈላጊውን እርዳታ በማስጠት ለወረርሽኝ ቁጥጥር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

በሽታውን ሪፖርት ወደ አደረጉ ሀገራት ሄዶ የበሽታውን ምልክቶች ማሳየት የጀመረ ሰውን የሚያውቅ ማንኛውምሰውበአቅራቢያውለሚገኝ የጤና ተቋምማሳወቅ ወይምከታች በተገለፁት አድራሻዎች በማጠቀምሪፖርት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ በነፃ የስልክ ማስመር 8335 ወይምበመደበኛ የስልክ ቁጥር 0118276796 ወይም በኢሜል አድራሻችን phemdatacenter@gmail.com ወይም ephieoc@gmail.com በማጠቀምማግኘት ይቻላል፡፡

የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት

ጥር 25, 2012 ዓ.ም.

አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ